# በዉሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር
# የውሃ ልማት ፈንድ ስራ አስፈጻሚ

## የ2015 በጀት አመት አመታዊ ዕቅድ

በመስከረም 2015 የተከለሰ
አዲስ አበባ

# Contents


1. **መግቢያ** ........ **1**

2. **የነባራዊ ሁኔታዎች ትንተና** ........ **1**

*2.1. የውጫዊ ሁኔታዎች ትንተና/ ከውሃ ልማት ፈንድ ስራ አስፈጻሚ ውጭ በዉሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር/* ........ *1*

*2.2. የውስጣዊ ሁኔታ ትንተና/ በውሃ ልማት ፈንድ ስራ አስፈጻሚ ውስጥ/* ........ *2*

3. **የ2014 በጀት ዓመት እቅድ አፈጻጸም** ........ **3**

**4. የእስትራቴጂክ አፈጻጸም ማዕቀፍ** ........ **5**

4.1. **ራዕይ፤ተልዕኮና እሴቶች** ........ **5**

***ራዕይ*** ........ *5*

***ተልዕኮ*** ........ *5*

***ዕሴቶች*** ........ *5*

*4.2 ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮችና ውጤቶች* ........ *5*

*3.1. ዋና ዋና ግቦች /በስራ አስፈጻሚው የሚከናወኑ/* ........ *5*

*3.2. በዋና ዋና ግቦች ሥር የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት* ........ *5*

***5.*** **የ2015 በጀት ዓመት በየምዕራፉ የሚከናወኑ ተግባራት** ........ **11**

*5.1 በዝግጅት ምዕራፍ የሚከናወኑ ተግባራት ፤* ........ *11*

*5.2 የትግበራ ምዕራፍ የሚከናወኑ ተግባራት ፤* ........ *11*

*5.3 የማጠቃለያ ምዕራፍ /በክትትልና ግምገማ ምዕራፍ የሚከናወኑ* ........ *12*

**የክትትል፣ ግምገማ እና የድጋፍ ሥርዓት** ........ **12**

6. **የእቅዱ ማስፈፀሚያ ስልቶች/የሚኒስትሪውን የማስፈጸሚያ ስልቶችን በመጠቀም ለስራ አስፈጻሚው ማዋል** ........ **13**

7. **የበጀት መጠንና ምንጭ** ........ **14**

**8. ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች እና ሊወሰዱ የሚገባቸው የመፍትሄ ሃሳቦች** ........ **14**

**9. ማጠቃለያ** ........ **15**

## 1. መግቢያ

የውሃ ልማት ፈንድ ጽ/ቤት ከውሃ ዘርፍ አስተዳደር ፖሊሲና ስትራቴጂ መርሆች አንዱ በሆነው ወጪን በማስመለስ መርህ /Cost Recovery Principle/ ላይ በመመስረት ለከተሞች የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን እና ለመስኖ ልማት ፕሮጄክቶች ማስፈጸሚያ በረጅም ጊዜና በአነስተኛ ወለድ የሚከፈል ብድር እንዲሰጥ ታስቦ በጥር ወር 1994 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 268/1994 የተቋቋመ መንግስታዊ ተቋም የነበረ ሲሆን። በ2014 በተደረገ የሚኒስቴር መስሪያቤቶችና የተጠሪ ተቋማት አዲስ መዋቀራዊ ማሻሻያ ጽ/ቤቱ በዉሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ስር የውሃ ልማት ፈንድ ስራ አስፈጻሚ በመሆን ስራዎቹን እያከናወነ ይገኛል።

የውሃ ልማት ፈንድ ስራ አስፈጻሚ (የቀደሞ ው/ል/ፈ ጽ/ቤቱ) ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 2014 በጀት አመት መጨረሻ ድረስ በስራ አስፈጻሚው (ጽ/ቤቱ) በብድር ፋይናንስ የተደረጉ የከተማ መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ፕሮጀክቶች ቁጥር 123 የደረሰ ሲሆን፣ የብድር መጠኑም እስከ ብር 28.06 ቢሊዮን ደርሷል። ከዚህም ውስጥ 23.47 ቢሊዮን ለመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ፋይናንስ ሲሆን 4.59 ቢሊዮን ደግሞ ለአዲስ አበባ ከተማ የሳኒቴሽን ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ፋይናንስ ነው። ከእነዚህ ፕሮጀክቶች መካከል ግንባታቸው ተጠናቆ ብድር መመለስ ከጀመሩ የውሃ አገልግሎት ድርጅቶች ላይ እስካሁን ድረስ ብር 903.77 ሚሊዮን ተመላሽ ተደርጓል።

## 2. የነባራዊ ሁኔታዎች ትንተና

የውሃ ልማት ፈንድ ስራ አስፈጻሚ/የቀድሞ ው/ል/ፈ ጽ/ቤት/ በ1994 ዓ/ም ተመስርቶ በ2014 ዓ/ም የኢትዮጵያ መንግስት ባካሄደው የመዋቅር ማስተካከያ ወደ ውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ተጠቃሏል። ይህን መሰረት በማደረግ የዉሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር በ2014 በጀት አመት አዲስ አደረጃጀት ያካሄደ ሲሆን በዚህ መሰረት የውሃ ልማት ፈንድ ስራ አስፈጻሚን በሶስት ዴስኮችን ማለትም የብድር ፈንድ አስተዳደር ዴስክ፣ የፈንድ ልማትና አፕሬዛል ዴስክና የተቋማት አቅም ግንባታ ዴስክ ተዋቅሯል። በዚህም መሰረት በአዲስ መልኩ የተደራጀውን በመቃኘት የሁኔታዎች ትንተና በስራ አስፈጻሚው ባለፉት ዓመታት የተደረጉ ጅምር ጥረቶችንና የተገኙ ተጨባጭ ለውጦች፤ የተለዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች፤ እንዲሁም መልካም አጋጣሚዎችን፤ ስጋቶችን ለይቶ በማውጣት መልካም አጋጣሚዎችን በአግባቡ በመጠቀም የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብና ስጋቶችን አስቀድሞ በመለየት በእቅዱ አፈጻጸም ላይ የሚያደርሱትን ተጽዕኖ ለመቀነስ ስለሚስችል ይህ የሁኔታዎች ትንተና ተዘጋጅቷል ።

### 2.1. የውጫዊ ሁኔታዎች ትንተና/ ከውሃ ልማት ፈንድ ስራ አስፈጻሚ ውጭ በዉሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር/

በውሃ ልማት ፈንድ ስራ አስፈጻሚ ተጨባጭ የብድር መጠጥ ዉሃ ልማት በማረጋገጥ የህብረተሰቡንና የከተሞችን ተጠቃሚነት በዘላቂነት ከማረጋገጥ አኳያ ክንውኖቹ የሚሰከትሏቸው ውጤቶች በስራ አስፈጻሚው ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩበት የሚችል መሆኑ የታወቀ ነው። በመሆኑም ለውሃ ልማት ፈንድ ስራ አስፈጻሚ አጋዥ የሆኑ መልካም አጋጣሚዎች በመለየት ለለውጥና ለልማት እንቅስቃሴዎች አጋዥ እንዲሆኑና በስጋትነት የሚታዩ ሁኔታዎችንም በመገንዘብ የሚያሳድሩትን ተጽዕኖ መቋቋም እንዲቻል ወይም በብድር መጠጥ ዉሃ ልማት ላይ የከፋ ጉዳት እንዳያስከትሉ የሚቻልበትን መንገድ አቅዶ ወደ ስራ መግባት አስፈላጊ በመሆኑ ያሉ መልካም አጋጣሚዎችንና ስጋቶችን በሚከተለው መንገድ ለመተንተን ተሞክሯል።

■ ምቹ ሁኔታዎች

- የአገሪቱና የሚኒስትሪው ከተሞችን በብደር የመጠጥ ዉሃ ግንባታቸውን እንዲያከናውኑ በፖሊሲ ማካተት፤
- የተለያዩ ከተሞችና የክልል አስተዳደሮች ለብድር የመጠጥ ዉሃ ልማት ተጠቃሚነት ያልቻው ፍላጎት ማደግ
- የብድር መጠጥ ዉሃና ሳኒቴሽን ለመደገፍ የልማት አጋራት ቁርጠኝነት መጨመር
- ሚኒስትሪው ስራ አስፈጻሚው ዕቅዱን ለማከናውን አስፍላጊ የሚባሉ ዴስኮችና ፕሮግራሞች መፍቀዱ
- የብድር መጠጥ ዉሃና ሳኒቴሽን ለማገዝ ሚኒስትሪው ከተለያዩ የመንግስት አካላት የተዋቀሩ ቦርድ ማቋቋሙ

■ ሥጋቶች

- የቅንጅታዊ አሰራር ያለው አረዳድ የተለያየ መሆኑና ከመጠጥ ዉሃ ስራ አስፈጻሚ ጋር ተቀራራቢነት ያለው መሆን፤
- በቂ ልምድና ክህሎት ያላቸዉ ባለሙያዎች በሚፈለገዉ መጠንና ዓይነት ያለማግኘትና የፍልሰት ችግር፤
- ለብድር ማስመለስ አስዋፅዖ ያላቸው የህግ ማዕቀፎች በአግባቡና በተፈለገው ፍጥነት ወደ ተግባር አለመለወጣቸው፤
- በየደረጃው ያለው የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ያልጎለበተ መሆን ፣

## 2.2. የውስጣዊ ሁኔታ ትንተና/ በውሃ ልማት ፈንድ ስራ አስፈጻሚ ውስጥ/

የውሃ ልማት ፈንድ ስራ አስፈጻሚ በከተሞች ያለውን የንጹህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ የማህበረሰቡን ጤንነትና የኑሮ ሁኔታ ከፍ በማድረግ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚያስችል ስራዎችን ያከናውናል። ከዚህ አንጻር በውሃ ልማት ፈንድ ስራ አስፈጻሚ በተቃኘ አሰራር ሂደት የተጀመሩ መልካም ጥረቶችን የበለጠ በማጠናከር በሚኒስቴር መስርያ ቤቱ በቀጣይ አጠቃላይ የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን ለማስመዝገብ በሚደረግ ጥረት ሰፊ ስራ መስራት ይጠይቃል። ይህን ለማሳካት በስራ አስፈጻሚው በአጠቃላይ በጥንካሬና በድክመት የተለዩ ውስጣዊ ሁኔታዎች እንደሚከተለው ቀርቧል።

■ ጠንካራ ጎኖች

- በስራ አስፈጻሚው ሲከናወኑ ከነበሩ ተግባራት በአዎንታዊ ትምህርት የሚወሰድባቸው አመላካች ልምድ መገኘቱ፣
- ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ለማዘመንና ዘመናዊ የመረጃ ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም የሚደረግ ጥረት
- በሰራተኛው መካከል ስራን በቡድን መንፈስ ለመስራት ቅንጅታዊ አሰራር ለማጠናከር ጥረት እየተደረገ መሆኑ፤

■ ደካማ ጎኖች

- በስራ አስፈጻሚው መስኩ የሚፈልገውን ክህሎትና ልምድ ያለው የሰው ኃይል ወደ ተቋሙ ለመሳብ የሚደረገው ጥረት፤
- በስራ አስፈጻሚው/ተቋሙ ክህሎትና ልምድ ያለው የሰው ኃይል እንዲኖር ዘላቂና ቀጣይነት ያለው የአቅም ግንባታ ስራዎች በሚጠበቀው ልክ አለመከናወናቸው ፤
- በስራ አስፈጻሚው በቀጣይ ለሚካተቱ ተጨማሪ የብደር ፕሮግራም የሚሆን በጀት ተቀርጾ የፈንድ ማፈላለጊያ እየተካሄደበት ቢሆንም እስከዚህ በጀት አመት ውጤታማ መሆን አለመቻል፤

## 3. የ2014 በጀት ዓመት እቅድ አፈጻጸም

የውሃ ልማት ፈንድ ስራ አስፈጻሚ (የቀደሞ ው/ል/ፈ ጽ/ቤቱ) ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 2014 በጀት አመት መጨረሻ ድረስ በስራ አስፈጻሚው (ጽ/ቤቱ) በብድር ፋይናንስ የተደረጉ የከተማ መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ፕሮጀክቶች ቁጥር 123 የደረሰ ሲሆን፣ ከእነዚህም ፕሮጄክቶች ውስጥ እስከ በጀት ዓመቱ መጨረሻ ድረስ 63 ፕሮጀክቶች ተጠናቀው ለኅብረተሰቡ አገልግሎት መስጠት የጀመሩ ሲሆን አራት ከተሞች ማለትም ጋምቤላ፣ ደንቢደሎ፣ ጨንቻና ያቤሎ በጽ/ቤቱ አሰራር ስራቸውን ሊያከናዉኑ ስላልቻሉ ወደ ሌላ ፕሮግራም እንዲዘዋወሩ ተደርጓል። ከተጠናቀቁት ከተሞች መካከል የ42ቱ ቀደም ሲል ወደ ብድር መመለሱ ምዕራፍ የተሸጋገሩ ሲሆን፣ ቀሪዎቹ ደግሞ በብድር ስምምነቱ መሰረት የችሮታ ጊዜያቸውን ሲጠናቀቅ በቀጣዮቹ ዓመታት ወደ ብድር መመለስ ምዕራፍ ለማሸጋገር ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል።

ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው በጽ/ቤቱ ብድር ፋይናንስ ከተደረጉት ጠቅላላ ፕሮጄክቶች ውስጥ 56 ፕሮጄክቶች በተለያየ የአፈጻጸም ደረጃ ላይ የሚገኙ ሲሆን እነዚህም፡-

✓ በዋን ዎሽ ፕሮግራም-1 ሲካሄዱ ከነበሩት የ20 ከተሞች የመጠጥ ውሀና ሳኒቴሽን በ2014 በጀት ዓመት በዋን ዎሽ ፕሮግራም-2 እንዲቀጥሉ የተወሰነላቸው 8 ከተሞች (ፊንጫዋ፣ ወሊሶ፣ ለገጣፎ፣ ዲላ፣ ሳውላ፣ ወራቤ፣ ታርጫ የፕሮጀክቶቹ) ሲሆኑ የያቤሎ ፕሮጀክት በኢመርጀንሲ/emergency wash/ እንዲካተት በመወሰኑ የሰባቱ ፕሮጀክት በመከናወን ላይ ይገኛል።

በመሆኑም በደቡብ ክልል ከሚገኙ 4ቱ መካከለኛ ከተሞች ማለትም፡-

- የዲላ ከተማ መጠጥ ዉሃ ፕሮጀክት ወደ ግንባታ ገብቶ 35 በመቶ ላይ ይገኛል።
- የሳውላ ከተማ መጠጥ ዉሃ ፕሮጀክት ወደ ግንባታ ገብቶ 40 በመቶ ላይ ይገኛል።
- የታርጫ ከተማ መጠጥ ዉሃ ፕሮጀክት ወደ ግንባታ ገብቶ 45 በመቶ ላይ ይገኛል።
- የወራቤ ከተማ መጠጥ ዉሃ ፕሮጀክት ወደ ግንባታ ገብቶ 1 በመቶ ላይ ይገኛል።

እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል ከሚገኙት አራት መካከለኛ ከተሞች ማለት፡-

- የፊንጫዋ ከተማ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ወደ ግንባታ ገብቶ 20 በመቶ ላይ ይገኛል።
- የወሊሶ ከተማ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ወደ ግንባታ ገብቶ 6.6 በመቶ ላይ ይገኛል።
- የለገጣፎ ከተማ የመጠጥ ዉሃ ፕሮጀክቶች የጨረታ ሂደት ላይ ይገኛሉ።
- የያቤሎ ከተማ የመጠጥ ዉሃ ፕሮጀክቶች ወደ ኢመርጀንሲ/emergency wash/ እንዲካተት ተደርጓል።

✓በአፍሪካ ልማት ባንክ አዳማ ቢቸና ጎዴ እና መቐለ ከተማ የመጠጥ ውሃና ፕሮጀክቶች የተካተቱ ሲሆኑ፡

- የአዳማ ከተማ መጠጥ ዉሃና ሳኒቴሽን ፕሮጀክት በወሰን ማስከበር ችግር፤ በኮረና ወረርሽኝ እና በአማካሪ ተቋራጭ ደካማ አፈፃፀም ምክንያት የፕሮጀክቱ አፈጻጸም 20.5 በመቶ ላይ ይገኛል።
- የብቸና ከተማ የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ፕሮጀክት የሲቪል ስራ ግንባታ 100% የተከናወነ ቢሆንም የዋና የግፊት መስመር እና የኤሌክትሮሜካኒካል የተጨማሪ ስራዎች በመከናወን ላይ የሚገኙ ሲሆን የኤ/መካኒካል ስራዎቹ ከ50% በላይ ተጠናቋል።
- የመቐለ ከተማ የመጠጥ ውሃ እና ሳኒቴሽን ፕሮጀክት በክልሉና በፌዴራል መንግስት በተፈጠረው አለመግባባት፤ለጂንጂ እና ለመገጣጠሚያ አቅርቦት የሚዉል ኤል.ሲ በክልሉ በኩል በወቅቱ ባለመከፈቱ እና የኤሌክትሮሜካኒካል ግዥ ዳግም ጨረታ ወጥቶ በክልሉ በኩል ተገምግሞ በወቅቱ ባለመቅረቡ የተነሳ አፈፃፀሙ በ28.8% ላይ ይገኛል።
- የጎዴ ከተማ መጠጥ ዉሃና ሳኒቴሽን ፕሮጀክት ተጠናቆ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

✓የአንድ ቅርጫት ፈንድ/ Basket Fund/ ፕሮግራም ሥር አርባ ስምንት (48) ከተሞች የተካተቱ ሲሆን የ10ሩ ከተሞች/ አዲግራት፣ ማይጨው፣ ሶዶ፣ቦንጋ፣ ገርበጉራቻ፣ ሆለታ፣ ፍቼ፣ ደንቢደሎ፣ ወልድያና ቃዋቀቶ/ ፕሮጀክቶች በባለፉት ጊዜያት ተጠናቀው አገልግሎት እየሰጡ ሲሆን ፡፡

- ቀሪዎቹ 29 ፕሮጄክቶች/ ከአማራ ክልል (ሀይቅና አረርቲ) ፣ ከኦሮምያ ክልል (ዶዶላ፣ ሰቃ፣ ኢጀሬ፣ አርቦዬ፣ ደ/ጽጌ፣ ሳጉሬ፣ አዋሽ፣ ቂምባቤ፣ አዳባ፣ ሆኝዱሬ፣ ኮምቦልቻ፣ ቱሉሚልኪና ሸቂ)፣ ከደቡብ ክልል(ቢንሺቾ፣ ጂንካ፣ ሻንቶ፣ ብኢ፣ ገደብ፣ ዳሎቻ፣ ሾኔ፣ ቀያፈር፣ ኪሌና ዝፍኔ)፣ ከሲዳማ ክልል ቀባዶ፣ ከደ/ምዕራብ (ጌቻ፣ ዋቻና ያሎላላ)/ ፕሮጀክቶች በግንባታ ላይ ሲሆኑ ሌሎች 9 የሚጠጉ ፕሮጀክቶች በተለያየ የቅድመ ግንባታ ስራዎች ላይ ይገኛሉ፡፡

✓በኩዌት ፈንድ የሚከናወነዉ የአክሱም ከተማ መጠጥ ዉሃና ሳኒቴሽን ፕሮጀክት የዉሃ መገኛዉ የገፀ ምድር ዉሃ በመሆኑ የዉሃ ማጠራቀሚያ (ሪዘርቫየር) ግድብ የሚገነባለት ፕሮጀክት ነዉ፡፡ ፕሮጀክቱ ከተጀመረ ረዘም ያለ ጊዜ የወሰደ ቢሆንም ቀደም ሲል በነበረው የትግራይ ክልል መንግሥት የውሃ ቢሮ የአሰራርና አፈጻጸም ችግሮች የተነሳ የፕሮጄክቱ እንቅስቃሴ ወደኋላ ሊጓተተ ችሏል፡፡ አሁን ባለዉ የስራ እንቅስቃሴዉ የመጨረሻ ድራፍት የጥናትና ዲዛይን ሪፖርት (Final Draft Study & Design Report) ቀርቦ በመገምገም ላይ ይገኛል፡፡ ነገርግን የክልሉ የጸጥታ ሁኔታ ቀጣይ ስራዎችን ለማከናወን እንቅፋት ሁኗል፡፡

✓በቻይናው ኤግዚም ባንክ የብድር ድጋፍ እየተከናወነ የሚገኘዉ የመቐሌ ከተማ መጠጥ ዉሃ የግባ ፕሮጀክት ሲሆን በክልሉ በተፈጠረዉ የፀጥታ ችግር ምክንያት የግንባታዉ  አፈፃፀም በ17% ላይ ይገኛል፡፡በቅርብ ጊዜ ፌደራልና የክልሉ ዉሃ ቢሮ የበላይ ሃላፊዎች፣ አማካሪ እና ተቋራጭ በተገኙበት በተደረገ ዉይይት ስራዉን ለማስቀጠል በተደረሰበት ስምምነት መሰረት ስራውን እንደገና ለማስጀመር የወደሙ ንብረቶችን የመለየትና ጥገና የሚያስፈልጋቸውን ንብረቶች ለማስጠገን በእንቅስቃሴ የተደረገ ቢሆንም አሁን ባለው ሁኔታ ቀጣይ ስራዎችን ለማከናወን አልተቻለም፡፡

✓የሪቮልቪንግ ፈንድ ፕሮግራም ወደ ስድስት የሚጠጉ ፕሮጀክቶች የተካተቱ ሲሆን ፡-

- የኮምቦልቻ (አማራ) መጠጥ ዉሃ ፕሮጀክት ቀደም ሲል የነበረው የባለቤትነት ጥያቄ ችግር ተፍትቶ የግንባታ ኮንትራክተር ቀጥሮ 10%  ግንባታዉን አከናውኖ ይገኛል፡፡
- የአሶሳ ከተማ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት በጉድጓድ ቁፋሮ ሂደት ላይ የሚገኝ ሲሆን የሲቪል ስራዎችን ለመቅጠር የጨረታ ዶክመንቶች እየተዘጋጁ ይገኛሉ፡፡
- የሚዛን አማን ከተማ የፕሮጀክቱን ጥናት የሚያከናዉን አማካሪ ተቀጥሮ የጥናትና ዲዛይን ስራዎችን እያከናወነ ይገኛል፡፡
- የጎንደር ከተማ የጥልቅ ጉድጓድ ቁፋሮና እና ሲቪል ስራ/ኤ/መካኒካል/ ጨረታ ለማውጣት በቅድመ ዝግጅት እንቅስቃሴ ሂደት ላይ ይገኛል፡፡
- የደብረማርቆስ የመጠጥ ዉሃ ፕሮጀክት በባስኬት ፈንድ የተያዘዉ ዕቅድ በመዘግየቱ ምክንያት ፕሮጀክቱ በሁለት ፕሮግራም እንዲከናወን በቦርድ በተወሰነዉ መሠረት ደ/ማርቆስ ፕሮጀክት-2 ግንባታዉ ተጀምሮ 60% የደረሰ ሲሆን ደ/ማርቆስ ፕሮጀክት-1 ጨረታው በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል፡፡
- የድሬዳዋ ምዕራፍ 3 የጉድጓድ ቁፋሮ ስራ (አምስት ጥልቅ ጉድጓድ ቁፋሮ) ሙሉ በሙሉ ተጠናቆ የኤል/መካኒካል ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡

በውሀ ልማት ፈንድ ስራ አስፈጻሚ በብድር ፋይናንስ እየተደረጉ ያሉት ፕሮጀክቶች በዋነኛነት በሚሊዮኖች ለሚቆጠረው የከተማ ነዋሪ ህዝብ በቀጥታና በተዘዋዋሪ የንጹህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ከማድረጋቸው ጎን ለጎንም ለበርካታ አማካሪ ድርጅቶች፣የሥራ ተቋራጮች፣የዕቃ አቅራቢ ድርጅቶች እንዲሁም ለተለያዩ ባለሙያዎችና የህብረተሰብ ክፍሎች ከፍተኛ የስራ ዕድል የፈጠሩ እና በቀጣይነትም ተጨማሪ የሥራ ዕድሎች እንደሚፈጥሩ ይጠበቃል፡፡

## 4. የእስትራቴጂክ አፈጻጸም ማዕቀፍ

### 4.1. ራዕይ፣ተልዕኮና እሴቶች

**ራዕይ**

በ2022 የተቀናጀ ውሀ ሀብት አሰተዳደር ተዘርግቶ የመጠጥ ውሀና የኢነርጂ አቅርቦት ለሁሉም ዜጋ ተረጋግጦባት በብልጽግና ጎዳና የምትጓዝ ኢትዮጵያን ማየት፤

**ተልዕኮ**

የውሃና ኢነርጂ ሀብታችንን በፍትሃዊነት፣በዘላቂነትና በተቀናጀ መልኩ በማልማትና በማስተዳደር የዜጐችን የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን አቅርቦት፤ የኢነርጂ ፍላጐትና ሁለንተናዊ ሕይወት መሻሻልን ማረጋገጥ፤

**ዕሴቶች**

- ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት
- አዲስ ሃሳብና ፈጠራ
- እኩል ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት
- ፅናትና ቁጭት
- አካባቢ ጥበቃና ዘላቂ ልማት
- ሁልጊዜ መማር
- የቡድን ሥራ
- የሥራ ሥነ-ምግባር
- ሙስናና ብልሹ አሠራርን መጸየፍ

### 4.2 ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮችና ውጤቶች

ከ2013-2022 ዓ/ም ድረስ ላለው ስትራቴጂያዊ የእቅድ ዘመን በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ስትራቴጂያዊ ትኩረት መስኮች እና ከየትኩረት መስኩ የሚጠበቁት ስትራቴጂአዊ ውጤቶች ያቀደ ሲሆን። በመጠጥ ዉሃና ሳኒቴሽን ዘርፍ የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ተደራሽነት ማረጋገጥ በሚል ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስክ ያደገ የመጠጥ ውሃና የሳኒቴሽን ተደራሽነት ስትራቴጂያዊ ዉጤት አቅዶ እየተንቀሳቀሰ ሲሆን የስራ አስፈጻሚው የስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮችና ውጤቶች እንደሚከተለው ታቅዷል።

| ተ. ቁ | ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች | ስትራቴጂያዊ ውጤቶች |
|---|---|---|
| 1. | የተፋሰስ ልማት እና ዘላቂ የውሃ ሀብት አስተዳደር | ዘላቂነቱ የተረጋገጠ የውሃ ሀብት አስተዳደር፣ |
| 2. | የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ተደራሽነት ማረጋገጥ | ያደገ የመጠጥ ውሃና የሳኒቴሽን ተደራሽነት |
| 3. | ፈጣን ኢነርጂ ልማትና ተደራሽነት ለሁሉም ዜጎች | ያደገ የኢነርጂ ተደራሽነትና ተጠቃሚነት |

### 3.1. ዋና ዋና ግቦች /በስራ አስፈጻሚው የሚከናወኑ/

| ግብ | ዋና ዋና ግቦች | ግብ | ዋና ዋና ግቦች |
|---|---|---|---|
| 1 | የህብረተሰቡንና የባለድርሻ አካላትን ግንዛቤና ተሳትፎ ማሳደግ | 7 | የሰው ሀብት ውጤታማነትን ማሳደግ |
| 2 | የፋይናንስ አቅርቦትና አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ | 14 | የንፁህ መጠጥ ውሀ አቅርቦት ሽፋንን ማሳደግ |
| 3 | የባለዘርፈ ብዙ ጉዳዮች አካታችነትና ተጠቃሚነትን ማሳደግ | 15 | ሀገራዊ የሳኒቴሽን አገልግሎቱን ማሳደግ |
| 4 | የመረጃ አያያዝ አደረጃጀትና ልውውጥ ስርዓትን ማጎልበት | 17 | ተቋማዊ የመፈጸምና የማስፈጸም አቅምን ማሳደግ |
| 5 | የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚነትን ማሳደግ | 18 | የብድር ፋይናንስ ተጠቃሚ ከተሞችን ማሳደግ፣ |
| 6 | የአሰራር ስርዓት ቅልጥፍና ማሻሻል | 19 | የብድር ተሰብሳቢ አቅምን ማሳደግ |

### 3.2. በዋና ዋና ግቦች ሥር የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

የበጀት ዓመቱ ዕቅድ በዋነኛነት የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸምን በመገምገም እንዲሁም ለ2015 በጀት ዓመት በሚኒስቴር መስርያቤቱ ከተቀመጠው ዕቅድ፣ ስትራቴጂክ ግቦች እና ግቦቹን ለማሳካት በበጀት ዓመቱ የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት ዕቅድ እንዲያሳይ ተደርጎ ተዘጋጅቷል። የእያንዳንዱ ዋና ተግባር ዕቅድ የአፈፃፀም መለኪያ፣ ለእቅዱ የተሰጠ ክብደት፣ ዒላማና ዕቅዱ የሚፈፀምበትን ጊዜ እንዲያካተት ተደርጓል።

**ግብ 1፡- የህብረተሰቡንና የባለድርሻ አካላትን ግንዛቤና ተሳትፎ ማሳደግ**

- የመገናኛ ብዙሃንን በመጠቀም (በልማት ቦታ ጉብኝትና በዶክመንተሪ ፊልም) የው/ል/ፈ ስራ አስፈጻሚን 4 መረጃዎች በህ/ግ/ኮ/ስ/አ በኩል ተደራሽ ለማድረግ ዕቅድና ድጋፍ ማከናወን
- የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ድረ ገጽና ማህበራዊ ሚዲያ በመጠቀም የው/ል/ፈ ስራ አስፈጻሚን 10 መረጃዎች በህ/ግ/ኮ/ስ/አ በኩል እንዲሰራጩ ዕቅድና ድጋፍ ማከናወን
- የውሀ ልማት ፈንድ ብድር ተጠቃሚ ከተሞች ለብድር ማሟላት ስለሚገባቸው ጉዳዮች 1 ግንዛቤ ማስጨበጥ ማካሄድ
- ብድር መመለስ በጀመሩና በግንባታ ላይ ላሉ ከተሞች ብድር አአሰጣጥና አመላለስን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት ጋር የግንዛቤ ማስጨበጫ 2 መድረክ ማዘጋጀት
- በተዘጋጀው ስታንዳርድ መሰረት አገልግሎት አሰጣጥ እየተሰጠ መሆኑን አንድ ግዜ የተገልጋይ የእርካታ ዳሰሳ የስራ አስፈጻሚዉን ጥናት ማካሄድ

ግብ 2. **የፋይናንስ አቅርቦትና አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ**

- የመደበኛና ካፒታል በጀት ዝርዝር ወርሃዊና የሩብ ዓመት ካሽፍሎው ዕቅድ አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ የፋይናንስ ስራ አስፈጻሚ በማቅረብ የተጠየቀው ገንዘብ ከገንዘብ ሚኒስቴር ገቢ መሆኑን መከታተል
- ለአዳዲስ ከተሞች የመጠጥ ውሀና ሳኒቴሽን ፐሮጄክቶች ማስፈጸሚያ ከተለያዩ የፈንድ ምንጮች የቀረበ 466.1 ብድር
- ከተለያዩ የፋይናንስ ምንጮች ለብድር ስራ የተፈቀደ 3.10 ቢለየን ፈንድ/በጀት ማሰባሰብና ገቢ ማድረግ፣
- በበጀት ዓመቱ ቀደም ሲል ቃል የተገባውን የፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የሚሆን የመዋጮ ገንዘብ(matching fund) ብር 1.450 ቢለየን ሰብስቦ ገቢ ማድረግ፤
- በብድር ፋይናንስ ከሚደረጉ የተለያዩ ፕሮጀክቶች የሚቀርቡ የክፍያ ጥያቄዎችን በስምምነቱ መሠረት አጣርቶ በካሽፍሎው፣በቀጥታ ክፍያ እና የባንክ መተማመኛ ሰነድ (L/C) ክፍያ ዘዴዎችን በመጠቀም ብር 3.55 ቢሊየን ክፍያ መፈጸም፣
- የፕሮጀክቶችንና የመደበኛ በጀት አፈጻጸሞችን 6 ጊዜ ክትትልና ግምገማ ማከናወን፤
- የግዥ ፍላጎት እቅድ ማዘጋጀትና በግዝ አጽዳቂ ኮሚቴ ማጸደቅ

ግብ 3. **የባለዘርፈ ብዙ ጉዳዮች አካታችነትና ተጠቃሚነትን ማሳደግ**

- የሴቶች፣ የወጣቶችና ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች (ህጻናት፣አካል ጉዳተኞች፣አረጋውያን) በሚገነቡ ፕሮጀክቶች ላይና ከተገነቡ ብኋላ የሚኖራቸው ተሳታፊነትንና ተጠቃሚነትን በክትትልና በግምገማ ማረጋገጥ

ግብ 4. **የመረጃ አያያዝ አደረጃጀትና ልውውጥ ስርዓትን ማጎልበት**

- የኮምፒዩተር፣ ፕሪንተርና ተዛማጅ ዕቃዎች /hardware & software ብልሽት ማስተካከልና ጥገና ማድረግ፤
- ለተቋማት አቅም ግንባታ የሚሆን የዳታ ሴንተር በባለሙያ ማደራጀት
- የስራ አስፈጻሚውን የ10 ዓመት እና የ5 ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ ከአዲሱ የሚ/ር መስሪያ ቤቱ ስልጣንና ተግባር አንጻር መከለስ፣
- የስራ አስፈጻሚውን የ2014 በጀት ዓመት የ4ተኛው ሩብ ዓመት የፕሮግራም በጀት ሪፖርትና 2015 በጀት ዓመት የየሩብ ዓመት የፊዚካል እና የፕሮግራም በጀት ሪፖርት ማዘጋጀት
- የስራ አስፈጻሚውን የ2015 በጀት ዓመት ፊዚካል እና ፕሮግራም በጀት ዓመታዊ የድርጊት መርሃ ግብር ማዘጋጀት

ግብ 5. **የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚነትን ማሳደግ**

- የፕሮጀክት ብድር ሂሣብን ባኢፍሚስ መሥራት የሚቻልበት አማራጭ ካለ ለመጠቀም ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር መመካከርና ወደ ትግበራ መሸጋገር
- ቀደም ሲል ለበድር ሂሣብ መመዝገቢያ የሚሆን ሶፍት ዌር ለማዘጋጀት የሚያገለግል/TOR መሠረት አማካሪዎችን መቅጠር

**ግብ 6. የአሰራር ስርዓት ቅልጥፍና ማሻሻል**

- በፈንዱ ብድር አሰጣጥና አመላለስ ሥርዓት ላይ የሚታዩ የአሰራርና የህግ ክፍተቶችን በጥናት ለይቶ የማሻሻያ ሥራዎችን ማከናወን
- የሥራ ክፍሉን አላቂና ቋሚ ንብረቶች በአግባቡና ውጤታማ በሆነ መንገድ መጠቀም
- በውሃ ልማት ፈንድ የተዘጋጁ የአሰራር ማንዋሎች በስራ ላይ እንዲውል ክትትል ማድረግ

**ግብ 7.የሰው ሀብት ውጤታማነትን ማሳደግ**

- በየስራ አስፈጻሚው ለተመደቡ ባለሙያዎች የዴስኩን ተግባር፣ ኃላፊነት፣ የአሰራር መመሪያዎችን ማስተዋወቅ
- በየስራ አስፈጻሚው ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ሥልጠና ፍላጎት ዳሰሳ በማካሄድ ሥልጠና እንዲያገኙ ማመቻቸት፣
- በየስራ አስፈጻሚው ባለሙያዎች አፈጻጸም በመረጃ አስደግፎ መገምገም
- የሚ/ር መ/ቤቱን የማስፈጸም አቅም ለማጠናከር በግልና በጋራ /Individual Group Training/ የአጭር ጊዜ የአቅም ግንባታ ስልጠናችን እና የልምድ ልውውጦች የማመቻቸት ተግባር፤

**ግብ 14፡- የንፁህ መጠጥ ውሀ አቅርቦት ሽፋንን ማሳደግ**

14.1. **የአየር ንብረት ለውጥ የሚቋቋም ፕሮጀክት**

14.1.2. **በ CWA-II በጀት የሚደገፉ ፕሮጀክቶች**

- የ3 ከተሞችን የመጠጥ ውሃ ግንባታ ከደረሱበት አማካኝ 34.33% ወደ 100% እንዲደርሱ የክትትልና ድጋፍ ስራዎች ማከናወን
- የ2 ከተሞችን የመጠጥ ውሃ ግንባታ ከደረሱበት አማካኝ 7.5% ወደ 78% እንዲደርሱ የክትትልና ድጋፍ ስራዎች ማከናወን
- የ1 ከተማ የመጠጥ ውሃ ግንባታ ከደረሱበት አማካኝ 6.6 % ወደ 70% እንዲደርሱ የክትትልና ድጋፍ ስራዎች ማከናወን
- የ2 ከተሞችን የመጠጥ ውሃ ግንባታ ከደረሱበት አማካኝ 0.0 % ወደ 10% እንዲደርሱ የክትትልና ድጋፍ ስራዎች ማከናወን
- የ8 ፕሮጀክቶች ሪፖርቶችን በመገምገም፣ የሚያጋጥሙ ችግሮችን መፍታትና ግብረ- መልስ መስጠት
- ከአማካሪና ከስራ ተቋራጮች የሚቀርቡ 24 ክፍያዎችን በመመርመርና በማጽደቅ ለሚመለከተው ክፍል ማስተላለፍ
- የፕሮጀክቶችን ሂደትና ሁኔታ ግምገማና አውደ ጥናት ማካሄድ

14.2. **የአንድ ቋት መጠጥ ውኃ ፕሮጀክት**

14.2.1. **በብድር ፋይናንስ የሚከናወኑ የከተማ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች**

14.2.1.1. **በባስኬት ፈንድ ፋይናንስ የተደረጉ ፕሮጀክቶች**

- የ15 ከተሞችን የመጠጥ ውሃ ግንባታ ከደረሱበት አማካኝ 62.93% ወደ 100% እንዲደርሱ የክትትልና ድጋፍ ስራዎች ማከናወን
- የ6 ከተሞችን የመጠጥ ውሃ ግንባታ ከደረሱበት አማካኝ 16.08% ወደ 81.0% እንዲደርሱ የክትትልና ድጋፍ ስራዎች ማከናወን
- የ7 ከተሞችን የመጠጥ ውሃ ግንባታ ከደረሱበት አማካኝ 5.92% ወደ 59.57% እንዲደርሱ የክትትልና ድጋፍ ስራዎች ማከናወን
- የ10 ከተሞችን የመጠጥ ውሃ ግንባታ ከደረሱበት አማካኝ 0.20 % ወደ 27.5% እንዲደርሱ የክትትልና ድጋፍ ስራዎች ማከናወን
- የ38 ፕሮጅክቶች ሪፖርቶችን በመገምገም፣ የሚያጋጥሙ ችግሮችን መፍታትና ግብረ- መልስ መስጠት
- ከአማካሪና ከስራ ተቋራጮች የሚቀርቡ 76 ክፍያዎችን በመመርመርና በማጽደቅ ለሚመለከተው ክፍል ማስተላለፍ
- የፕሮጀክቶችን ሂደትና ሁኔታ ግምገማና አውደ ጥናት ማካሄድ

14.2.1.2. **በአፍሪካ ልማት ባንክ ፋይናንስ የተደረጉ ፕሮጀክቶች**

- የአንድ ከተማን የመጠጥ ውሃ ግንባታ ከደረሰበት 65% ወደ 100% እንዲጠናቀቅ የድጋፍና ክትትል ስራዎችን ማከናወን
- የ2 ከተማን የመጠጥ ውሃ ግንባታ ከደረሰበት 24.1% ወደ 46.5% እንዲደርስ የድጋፍና ክትትል ስራዎችን ማከናወን
- የ3 ፕሮጅክቶች ሪፖርቶችን በመገምገም፣ የሚያጋጥሙ ችግሮችን መፍታትና ግብረ- መልስ መስጠት
- ከአማካሪና ከስራ ተቋራጮች የሚቀርቡ 12 ክፍያዎችን በመመርመርና በማጽደቅ ለሚመለከተው ክፍል ማስተላለፍ
- ፕሮጀክቶችን ክትትልና ግምገማ ከባለድርሻ አካላት ማካሄድ (የአዳማ ከተማ የክትትል ቡድን)

14.2.1.3. **በተዘዋዋሪ ፈንድ ፋይናንስ የተደረጉ ፕሮጀክቶች**

- የ2 ከተሞችን የመጠጥ ውሃ ግንባታ ከደረሱበት አማካኝ 75.4% ወደ 100% እንዲደርስ የድጋፍና ክትትል ስራዎችን ማከናወን
- የ1 ከተማ የመጠጥ ውሃ ግንባታ ከደረሰበት 7.5% ወደ 80% እንዲደርስ የድጋፍና ክትትል ስራዎችን ማከናወን
- የ3 ከተሞችን የመጠጥ ውሃ ግንባታ በማካኝ 23.30% እንዲደርሱ የድጋፍና ክትትል ስራዎችን ማከናወን
- የ3 ፕሮጅክቶች ሪፖርቶችን በመገምገም፣ የሚያጋጥሙ ችግሮችን መፍታትና ግብረ- መልስ መስጠት
- ከአማካሪና ከስራ ተቋራጮች የሚቀርቡ 18 ክፍያዎችን በመመርመርና በማጽደቅ ለሚመለከተው ክፍል ማስተላለፍ

14.2.1.4. **በኩዌት ፈንድ ፋይናንስ የተደረጉ ፕሮጀክቶች**

- የ1 ከተማ የመጠጥ ውሃ ግንባታ ከደረሰበት 0% ወደ 5% እንዲደርስ የድጋፍና ክትትል ስራዎችን ማከናወን
- የ1 ፕሮጅክቶች ሪፖርቶችን በመገምገም፣ የሚያጋጥሙ ችግሮችን መፍታትና ግብረ- መልስ መስጠት
- ከአማካሪና ከስራ ተቋራጮች የሚቀርቡ 2 ክፍያዎችን በመመርመርና በማጽደቅ ለሚመለከተው ክፍል ማስተላለፍ

14.2.1.5. **በኢግዚም ፈንድ ፋይናንስ የተደረጉ ፕሮጀክቶች**

- የ1 ከተማ የመጠጥ ውሃ ግንባታ ከደረሰበት 17% ወደ 20% እንዲደርስ የድጋፍና ክትትል ስራዎችን ማከናወን
- የ2 ፕሮጅክቶች ሪፖርቶችን በመገምገም፣ የሚያጋጥሙ ችግሮችን መፍታትና ግብረ- መልስ መስጠት
- ከአማካሪና ከስራ ተቋራጮች የሚቀርቡ 2 ክፍያዎችን በመመርመርና በማጽደቅ ለሚመለከተው ክፍል ማስተላለፍ

14.6. **በመጠጥ ውሃ አቅርቦት ዙሪያ የሚሰሩ የአካባቢ፣ማህበረሰብና አየር ንብረት ለውጥ/ በብድር ፋይናንስ የሚከናወኑ የከተማ የመጠጥ ውሃ**

- ተከልሰዉ ወይም ተጠንተው ለሚቀርቡ አዳዲስ የከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች የጥናትና ዲዛይን እንዲሁም አካባቢያዊ እና ማህበራዊ ጥናት ዶክመንቶችን በመፈተሽ ሙያዊ ድጋፍና አስተያየት መስጠት።
- በተለያዩ ፕሮግራሞች (ባስኬት ፈንድ፣አፍሪካ ልማት ባንክ፣ ዋን ዋሽና ተዘዋዋሪ ፈንድ) በግንባታ ላይ ያሉ ፕሮጀክቶች የተለያዩ አካባቢያዊና እና ማህበራዊ አሉታዊ ተጽእኖዎች በታቀደው ESMP (Environmental & Social Management Plan) መሠረት የጉዳት መከላከያ እርምጃዎች (Mitigation Measures) እየተተገበሩ መሆናቸውን መከታተልና አስፈላጊውን ሙያዊ እገዛ ማድረግ።
- በውሃ ልማት ፈንድ የሚተገበሩ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች የውሃ ደህንነት እቅድ (Water Safety Plan) እንዲያዘጋጁና እንዲተገብሩ ለክልል ውሃ ቢሮዎች ሙያዊ ድጋፍ መስጠትና መከታተል።
- በውሃ ልማት ፈንድ የሚተገበሩ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ኢኮኖሚ CRGE (Climate Resilient Green Economy)ን ጽንሰ-ሀሳብ በዋናነት/በመደበኛነት (Mainsteam) በማድረግ እንዲታቀዱና እንዲተገበሩ ለክልል ውሃ ቢሮዎች ሙያዊ ድጋፍ መስጠትና ድጋፍ ማድረግ።

**ግብ 15፡- ሀገራዊ የሳኒቴሽን አገልግሎቱን ማሳደግ**

15.1.6. **ለሚኒስቴር ሰራተኞች፣ ለክልል እና በፕሮጀክቱ ለታቀፉ የውሃ አገልግሎቶች የአቅም ግንባታ ስራዎች ማከናወን**

- ከውኃ እና ኢነርጂ ሚ/ር፤ከክልል የውኃ ቢሮ እንዲሁም ከተመረጡ የፕሮጀክት ከተሞች ከንቲባ የተወጣጣ 2 ተሳታፊዎችን ያካተተ ቡድን በሁለት ክላስተር በአህጉራዊና አለማቀፋዊ ከሳኒቴሽን ጋር በተገናኘ የውጭ አገር ሴሚናሮች እና ወርክሾፖ/ልምድ ልውውጦች ላይ እንዲሳተፉ በማድረግ የማስፈፀም አቅማቸውን ማጎልበት ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ።

- በGIS፤በWater GMS እንዲሁም በSewer GMS ሶፍትዌሮች እና በኮንትራት አስተዳደር ላይ ስልጠናዎችን ለ 5 ሰልጣኞች በአንድ ዙር መስጠት በሚሰጠው ስልጠና እንዲሳተፉ ማድረግ

15.1.7 **በጣልያን ልማት ድርጅት የሚገነቡ 6 የሳኒቴሽን ፕሮጀክቶች**

- የሳኒቴሽን አማካሪ ቅጥር ማካሄድ/መቅጠር
- በ6 ከተሞች የባለሙያና የእቃ ሞቢላይዜሽን መካሄዱን ማረጋገጥ
- በአማካሪ የቀረበ ኢንሰፕሽን ሪፖርት መገምገም
- በአማካሪ የቀረበ ድራፍት ሪፖርት መገምገም
- በአማካሪ የቀረበ የመጨረሻ ሪፖርት መገምገም፣ ማጸደቅና ወደ ቀጣይ ስራ እንዲቀርብ ማድረግ
- በአማካሪ የተዘጋጀውን የሳኒቴሽን የጨረታ  በመገምገም ወደ ጋዜጣ መላክ
- በበአማካሪ የተዘጋጀውን የሳኒቴሽን የጨረታ  ጋዜጣ የሚቀይበትን አየር ሰዓት መከታተል
- ተከልሰዉ ወይም ተጠንተው ለሚቀርቡ የስድስት ከተሞች የሳኒቴሽንና ሃይጂን ፕሮጀክቶች የጥናትና ዲዛይን እንዲሁም አካባቢያዊ እና ማህበራዊ ጥናት ዶክመንቶችን በመፈተሽ ሙያዊ ድጋፍና አስተያየት መስጠት።

**ግብ 17፡- ተቋማዊ የመፈጸምና የማስፈጸም አቅምን ማሳደግ**

**ለሚኒስቴር ሰራተኞች፣ ለክልል እና በፕሮጀክቱ ለታቀፉ የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ፕሮጀክቶች የሚሰጡ የአቅም ግንባታ ስራዎች ክትትልና ድጋፍ ማድረግ**

- በዩኒሴፍ ድጋፍ ለክልል ባለሙያዎች የአይ ኤስ ኦ በመጠጥ ውሃ ጥራት በሚሰጠው የሃገር ውስጥ ስልጠና በመሳተፍ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ
- ለ20 ከተሞች ለሚወጣጡ 80 በባለሙያዎች ሚሰጠውን  ሥልጠና በመሳትፍ መከታተልና መደገፍ
- ለ24 ባለሙያዎች በገጠር መጠጥ ውሃ ተቋማት እና በከተማ መጠጥ ውሃ በኦፕሬሽንና ጥገና ማንዋል ላይ በሚሰጠው ስልጠና በመሳትፍ ከተትልና ድጋፍ ማድረግ

**ለሚኒስቴር ሰራተኞች እና  ለክልል የኢነርጂ ዘርፍ ባለሙያዎች/ሰራተኞች የሚሰጡ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ክትትልና ድጋፍ ማድረግ**

- ለባዮጋዝ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች የአጠቃቀም እና ጥገና በሚሰጠው ስልጠና በመሳትፍ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ
- በኢነርጂ ቴክኖሎጂዎች ላይ ለአነስተኛ የኢነርጂ  የቴክኖሎጂ ኢንተርፕራይዞች የአመራረት ስልጠና ተሳታፊ መሆንና ክትትልና ድጋፍ ማድረግ
- ለባዮጋዝ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች የባዮጋዝ ተረፈ-ምርት(Bio-slurry) አጠቃቀም በሚሰጠው ተሳታፊ በመሆን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ

**ግብ 18፡- የብድር ፋይናንስ ተጠቃሚ ከተሞችን ማሳደግ፣**

- በብድር ፋይናንስ የሚደረት ከተሞችንና ተያያዥ የሆኑ የጥናትና ዲዛይን ሰነዶችን በመሰብሰብ የፕሮጀክቶች የአዋጭነት ግምገማ ማከናወን

- የጥናት ክለሳ ተከናዉኖ የሚቀርቡ የከተሞች የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ፕሮጀክቶች ሰነድ ላይ Project Rescoping and Re-appraisal ሥራዎችን በማካሄድ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሚመለከተዉ አካል ለዉሳኔ ማቅረብ
- የመጠጥ ዉሃ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ብድር ለማቅረብ ከውሃ አገልገሎት ድርጅቶች ጋር የመልሶ ማበደር የብድር ውል ስምምነት በማዘጋጀት መፈራረም፣

ግብ 19፡-የብድር ተሰብሳቢ አቅምን ማሳደግ

- የብድር ተሰብሳቢዎችን በወቅቱ በመሰብሰብ በበጀት ዓመቱ ውስጥ 373.62 ሚሊየን ብር መሰብሰብ
- ብድር በመመለስ ላይ የሚገኙ እና በቀጣይም መመለስ የሚጀምሩትን የውሃ አገልግሎቶች የመስክ ክትትል በማድረግ ሙያዊ ድጋፍና ምክር መስጠት
- ግንባታቸው ተጠናቀ ብድር መመለስ የጀመሩ 15 የውሃ አገልግሎቶችን ድርጅቶችን የአቅም ግንባታ ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፤

## 5. የ2015 በጀት ዓመት በየምዕራፉ የሚከናወኑ ተግባራት

### 5.1 በዝግጅት ምዕራፍ የሚከናወኑ ተግባራት ፣

- በመንግሥት የ10 ዓመት መሪ ልማት ዕቅድ ውስጥ በመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ዘርፍ የተቀመጡ አጠቃላይ ዓላማዎችን፣ ስትራቴጂክ አቅጣጫዎችንና ግቦችን እና የስራ አስፈጻሚዉን (የቀድሞ የው/ል/ፈ ጽ/ቤት) የ2013-2017 የውጤት ተኮር ስትራቴጂክ ዕቅድ እንዲሁም የ2014 በጀት ዓመት የስራ አስፈጻሚዉን (የቀድሞ የው/ል/ፈ ጽ/ቤት) ፕሮግራሞች ዕቅድ አፈፃፀም መሠረት በማድረግ የ2015 በጀት ዓመት ረቂቅ ዕቅድ ተዘጋጅቶ ለሚኒስቴር መስርያቤቱ ቀርቦ በሰነዱ ላይ በበቂ ሁኔታ ውይይት በማድረግ በዕቅዱ ውስጥ በተካተቱት ጉዳዮችና ታሳቢዎች ላይ መግባባት ላይ ይደረሳል፡፡

### 5.2 የትግበራ ምዕራፍ የሚከናወኑ ተግባራት ፣

- በዚህ ምዕራፍ የዕቅዱ ዋና ዋና ሥራዎች የሚከናወኑ ሲሆን እያንዳንዱ ባለሙያ፣ ቡድን እና የስራ አስፈጻሚው መሪ በተቀመጠው መጠን፣ የጊዜ ሠሌዳና የጥራት ደረጃ ሥራውን መፈጸም ይጠበቅበታል፡፡ በዚሁ መሠረት የዕቅድ አፈጻጸሙን የተሳካ ለማድረግ በተዘረጋው አደረጃጀትና አሠራር መሠረት የበላይ አመራሩና መካከለኛ አመራሩ ፈጻሚውን በመደገፍና በማብቃት የሚንቀሳቀስ ይሆናል፡፡
- በዚህ የትግበራ ምዕራፍ ለዕቅዱ የተሳካ አፈጻጸም የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን የማሟላት፣ፈጻሚ ባለሙያዎች በውጤታቸው እንዲረኩ አቅማቸው በየጊዜው እየተገነባ እያደገ እንዲሄድ ጥረት ይደረጋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ፈጻሚዎች በእርስ በእርስ መማማሪያ መድረክ ዕውቀትና ክህሎታቸውን እንዲለዋወጡ ልምድ እንዲያዳብሩ ይደረጋል፣ የህዝብ አገልጋይነት አመለካከት እንዲያጎለብቱም በሙብትና ግዴታዎቻቸው ዙሪያ የውይይት መድረኮች ይካሄዳሉ፡፡
- በ2015 የፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ዓመታዊ ዕቅድ ሠነድ ላይ በዝርዝር በተቀመጡት የክትትልና ግምገማ ስልቶች መሠረት በየደረጃው የታቀዱ ሥራዎችን በመከታተልና በመገምገም ወቅቱን የጠበቀ የአፈጻጸም ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው ተቀጣጣሪ አካላት እንዲቀርቡ ይደረጋል፡፡

## 5.3 የማጠቃለያ ምዕራፍ /በክትትልና ግምገማ ምዕራፍ የሚከናወኑ

*በዚህ ምዕራፍ በየጊዜው ክትትልና ግምገማ እየተደረገባቸው የመጡትን የፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሥራ እንቅስቃሴዎችና የተገኙ ውጤቶች በበጀት አመቱ ተጠቃለው የሚገመገሙበት ወቅት ሲሆን፣ በዝግጅት ምዕራፍ እና በትግበራ ምዕራፍ የተከናወኑ ሥራዎች የተከናወኑበት አግባብ፣የተገኙ ውጤቶችና መልካም ልምዶች፣ ያጋጠሙ ችግሮች/ ዕጥረቶች በዝርዝር የሚገመገሙበት ነው። ግምገማው በመገምገሚያ ቼክሊስት መሠረት በየደረጃው የሚከናወን ሆኖ የዕቅድ አፈጻጸሙ ያለበት ደረጃ በምክንያትና በውጤት በዝርዝር የሚዳሰስበትና የሚታይበት ይሆናል። በተቀመጠው የውጤት ተኮር ዕቅድ አፈጻጸም ምዘና ሥርዓት መሠረት የሚለዩ ግንባር ቀደም ፈጻሚዎች ዕውቅና የሚሰጥበትና የሚበረታቱበት፣ አሳማኝ በሆነ ምክንያት ደካማ አፈፃፀም ያስመዘገቡ ሠራተኞች የሚደገፉበት እንዲሁም በቂ ባልሆነ ምክንያት የሚፈለገውን ውጤት ባላመጡ ፈጻሚዎች ላይ ተመጣጣኝ እርምጃ የሚወሰድበት ሁኔታ ይፈጠራል።*

## የክትትል፣ ግምገማ እና የድጋፍ ሥርዓት

*የውሃ ልማት ፈንድ ጽ/ቤት የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማና ድጋፍ ሥርዓት ዘርግቶ በመትግበር ላይ ሲሆን ይኸውም የትግበራውን አፈጻጸም ከኢላማ ጋር በማነጻጸር ክፍተቱን የሚፈተሸበትና የሚጠበቁ ውጤቶች መገኘታቸው የሚረጋገጥበት ሥርዓት ሆኖ እየተሰራ ያለበት ነው። ክትትልና ግምገማው ቀጣይነት ባለው መልኩ በተወሰነ ጊዜ (በየወሩ፣ በየ3ወሩ፣ በየ6 ወሩ እና በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የሚካሄድ ይሆናል። ክትትልና ግምገማ የሚካሄደው በሶስቱ ደረጃዎች ሲሆን፡-*

*አንደኛው በዕቅድ ደረጃ የሚካሄድ ክትትልና ግምገማ ዕቅዱ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት የተዘጋጀው ዕቅድ ሁሉን አቀፍ፣ ግልጽ፣ ሁሉም በቀላሉ የሚረዱት፣ ተግባራዊ ሊደረግ የሚችልና ፈጻሚዎችን የሚያነሳሳ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚካሄድ ክትትልና ግምገማ ነው።*

*ሁለተኛው በትግበራ ሂደት የሚካሄድ ክትትልና ግምገማ በተወሰነ የጊዜ ገደብ የሚካሄድ ሲሆን፣ ዕቅዱ በታሰበው አኳኋን እየተተገበረና የታሰበው ውጤት እየመጣ መሆኑ የሚረጋገጥበትና ለሚታዩ የአፈጻጸም ክፍተቶች የማሻሻያ እርምጃ የሚወሰድበት ይሆናል።*

*ሶስተኛው የግምገማ ዓይነት የውጤት ማጠቃለያ ግምገማ የዕቅድ ትግበራ ውጤት፣ ለውጤቱ ቀጣይነትም የማሻሻያ አቅጣጫ የሚቀመጥበትና አፈጻጸሙ የሚለካበት ግምገማ ነው።*

*ከላይ የጠቀስናቸውን የክትትልና ግምገማ ደረጃዎችን በአግባቡ ለማሳካት ጽ/ቤቱ የሚከተሉትን ሶስት ዋና ዋና የክትትልና ግምገማ ሥርዓቶች ይጠቀማል።*

- ☞ ***ሪፖርት፡-*** *ወርሃዊና የየሩብ ዓመት ሪፖርቶች ከመዘጋጀታቸው በፊት ቀደም ሲል በተካሄዱ ውይይቶቹ ላይ ተለይተው የተቀመጡ የዕቅድ አፈጻጸም ዕጥረቶችን በተመለከተ ከተለያዩ አካላት የተሰጡ አስተያየቶችና አቅጣጫዎች ተግባራዊ ስለመሆናቸው፣ በምን ደረጃና ሂደት ላይ እንዳሉ ታይቶ ሪፖርት የሚቀርብበት የክትትልና ግምገማ ስርዓት ነው።*
- ☞ ***ግምገማ፡-*** *የታቀዱ ስራዎች በተያዘላቸው የጊዜ እና የገንዘብ መጠን ከተከናወኑ እና በክትትልና በሪፖርት መልክ ተደግፎ ከቀረቡ በኋላ የስራውን ውጤታማነት እና ስኬት መምጣቱን ለማወቅ የሚደረግ የምዘና ስርዓት ሲሆን ይህንን የምዘና ግምገማዊ ስርዓት ተከትሎ ውጤቱ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ መሆኑን ለመለየት የሚያስችለን ስርዓት ነው።*

☞ **ሱፐርቪዥን /የመስክ ክትትልና ድጋፍ ሥራዎች/፡-** በመስክ ደረጃ የሚፈጸሙ ተግባራትን በፕሮጄክት ሳይቶችና በክልል ቢሮዎች አካባቢ በአካል በመገኘት የሚሰጡትን ድጋፎችና ክትትሎችን የሚያካትት ሲሆን ይኸውም በፕሮጄክቶች ግንባታና ጉድጓድ ቁፋሮ፣ ከግዥ አስተዳደርና ከፕሮጄክቶች ዓመታዊ እቅድና ሪፖርት አቀራረብ እንዲሁም ከፕሮጄክቶች መዋጮና ከብድር አመላለስ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ የክትትልና ድጋፍ ስራዎች ይከናወንበታል፡፡

በዚሁ መሰረት በየደረጃው ያሉ አካላት ዕቅዱ ላይ በተቀመጠው የክትትልና የግምገማ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በክትትል የተገኙ ውጤቶችን መሰረት በማድረግ የግምገማ ሥራ ይከናወናል፡፡ ይህም ዕቅዱን በጊዜ ገደብ ለመስራት ከታቀደው ምን ያህሉ ከተጣለው ግብ አንጻር እንደተከናወነና የአፈጻጸም ስኬትና ችግሮች የሚገመገሙበት እና ለቀጣዩ ዕቅድ ክንውን የተሻለ ውጤት እንዲመዘገብ መሠረት የሚጣልበት ሥርዓት ነው፡፡

## 6. የእቅዱ ማስፈፀሚያ ስልቶች/የሚኒስትሪውን የማስፈጸሚያ ስልቶችን በመጠቀም ለስራ አስፈጻሚው ማዋል

- በመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ዘርፍ የሚከናወኑ ተግባራት ከክልል መስተዳድሮች፤ ከልማትና ምርምር ተቋማት እንዲሁም ከአጋር አካላትና ባለድርሻ አካላት ጋር ትስስር በመፍጠር፣ የቅንጅት ሥራን ማጎልበት፤
- በተቋሙ አዲስ አደረጃጀት መሰረት የሚከናወኑ ተግባራን በውጤት ተኮርነትና ውጤታማ የሰው፤ የፋይናንስና የሀብት አጠቃቀም ስርዓትን እንደ ዋና የለውጥ መሳሪያ መጠቀም ፤
- ቴክኖሎጂን በመጠቀም የመፈጸም አቅምን ማሳደግ ፤የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት መዘርጋት፤ቀልታፋ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር ማድረግ፤
- ተከታታይነት ያለው የምክክር መድረክ በማዘጋጀት በውሃ ሀብት አስተዳደር ፤በመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን እንዲሁም በኢነርጂ ልማት ዘርፍ ያሉትን መርሆዎች ግንዛቤ ማሳደግና ምርጥ ተሞክሮዎች በመቀመር የማስፋት ሥራዎችን መተግበር፤
- በመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ጥናት ፤ዲዛይንና ግንባታ፤በፕሮጀክቶች አስተዳደር ፤በግብዓት አቅርቦት ሂደት ያለውን የአቅምና የውጤታማነት ክፍተት ለመሙላት የእውቀት ክፍተቱ በትምህርት የሥነምግባር ክፍተቶች ደግሞ በአሰራር ስርዓት እንዲስተካከሉ ማድረግ ፤
- የወጡ ህጎችንና ደንቦችን ሥራ ላይ እንዲውሉ የግንዛቤ ማዳበሪያ ሥራዎችን ማከናወን፤
- በልዩ ልዩ ቦታዎች የሚገኙትን ምርጥ ተሞክሮዎች በመቀመርና በማስፋት በሁሉም አካባቢ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ፤
- በየደረጃው ያለውን የመረጃ ፍላጎትን በመፈተሸ የመረጃ ክፍተትን በመለየት ክፍተቱን ለመሙላት የሚያስችል ስልት በመቀየስ ተግባራዊ ማድረግ፡
- ከተለያዩ የባለድርሻ አካላት ጋር የጋራ አሠራር፣ የሪፖርትና የመረጃ ልውውጥ ወዘተ ተግባሮችን ማከናወን የሚያስችል ቅንጅትና ግንኙነትን ማጠናከር፣
- የሴቶችን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትን፣ የአካል ጉዳተኞችን ተደራሽነት የሚያረጋግጡና እንዲሁም ሌሎች ተሻጋሪ ሥራዎችን በእያንዳንዱ ዕቅድ ውስጥ በማካተት ትኩረት ሠጥቶ መተግበር፣

7. **የበጀት መጠንና ምንጭ**

ለ2015 በጀት ዓመት የታቀደውን ፊዚካል ዕቅድ ግቦችንና ዋና ዋና ተግባራትን ለመፈጸም በካፒታል እና በመደበኛ በጀት ከመንግስት ግምጃ ቤት፣ ከእርዳታና ብድር ለሚ/ር መስሪያ ቤቱ ተመድቦለታል፡፡ ለሚኒስትሪው ከታቀዱ በጀት የውሃ ልማት ፈንድ ስራአስፈጻሚ ከተለያዩ አበዳሪ አካላትና ከስራአስፈጻሚው ብድር ተመላሽ በተመደብ በጀት የ56 የመጠጥ ዉሃ ፕሮጀክቶችና የአንድ የሳኒቴሽን ፕሮጀክት ስራዎች እየተከናወኑ ሲሆን ለአንድ ዋሽ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ 0.729 ቢልዮን ብር፣ ለአንድ ቋት ፕሮግራም ማስፈጸሚያ 2.046 ቢልዮን ብር፣ ለአፍሪካ ልማት ባንክ ማስፈጸሚያ 0.444 ቢልዮን ብር፣ ለሪቮልቪንግ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ 297.42 ሚልዮን ብር፣ ለኢግዚም ባንክ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ 0.01 ሚልዮን ብር፣ ለሳኒቴሽን 30.6 ሚልዮን ብርና ለኩዌት ፈንድ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ 2.24 ሚልዮን ብር በጠቅላላ 3.550 ቢልዮን ብር ለ2015 በጀት አመት ተመድቧል፡፡

**ለውሃ ኢነርጂ ሚ/ር 2015 በጀት ዓመት የተመደበ በጀት**

| የበጀት ዓይነት | የበጀት ምንጭ | | | |
|---|---|---|---|---|
| የበጀት ዓይነት | ከመንግስት ግምጃ ቤት | ከዕርዳታ | ከብድር | ጠቅላላ የተመደበ በጀት |
| መደበኛ | 1,888,0000 | - | - | 1,888,000.00 |
| ካፒታል | - | | 3,550,000,000 | 3,550,000,000.00 |
| ድምር | 1,888,0000 | - | 3,550,000,000 | 3,551,888,000.00 |

## 8. ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች እና ሊወሰዱ የሚገባቸው የመፍትሄ ሃሳቦች

☞ ብድር ለሚጠይቁ አዳዲስ ከተሞች ለብድር የሚሆን ፈንድ/በጀት አለመኖሩ

- ለብድር የሚውል በጀት ለማግኘት ከውሃ መስኖና ኢነርጂ ሚ/ር መስሪያ ቤት እና ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በጋራ መስራት

☞ በመተግበር ላይ ያሉ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ገድብ እና የገንዘብ መጠን ባለመጠናቀቃቸው የተነሳ ለተጨማሪ ጊዜና ወጪ እየተዳረጉ መሆኑ፣

- ለፕሮጀክት አስፈጻዓሚ አካላት ጠንካራና ተከታታይነት ያለው ድጋፍና ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፣

☞ ብድር መክፈል የሚገባቸው ተበዳሪ ከተሞች በተለያየ ምክንያት ብድራቸውን መክፈል አለመቻላቸውና በዚህም የተነሳ ውዝፍ ያለባቸው ከተሞች እየበዙ መምጣታቸው፣

- የብድር ተሰብሳቢን በወቅቱ ለማስመለስ የሚረዱ የክትትልና ድጋፍ ስራዎችን በተጠናከረ መልኩ መስራት የሚገባው መሆን ይኖርበታል፣

☞ በጽ/ቤቱ ለሰራተኞች ማትጊያ የሚሆን አሰራር ስርዓት ያልተዘረጋ በመሆኑ የሰራተኞች ፍልሰት እየጨመረ መሆኑ

- የጽ/ቤቱን የስራ አካባቢ የተረጋጋ እና ውጤታማ የሆነ ተቋም ለማድረግ የሚረዱ የማትጊያ አሰራሮችን መዘርጋት የሚገባው መሆኑ

## 9. ማጠቃለያ

የቀድሞ የውሃ ልማት ፈንድ ጽ/ቤት በበጀት ዓመቱ መዋቅራዊ አደረጃጀቱን፣ ተቋማዊ የማስፈጸም አቅሙን ሊያሻሽሉ የሚችሉ ስራዎችን በመስራት፣ ያሉትን የህግና የአሰራር ክፍተቶች እንዲሻሻሉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት እና የአሰራር ስርዓትን በማጠናከር ቀደም ሲል ተጀምረው በመካሄድ ላይ የሚገኙ ፕሮጄክቶች በወቅቱ እንዲጠናቀቁ የክትትልና ድጋፉን አገልግሎት በተጠናከረ መልኩ መስራት እንደሚኖርበትና አዲስ የብድር ጥያቄ ላቀረቡ ከተሞች ደግሞ የብድር ፋይናንስ ጥያቄያቸውን ለማሟላት አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን ማከናወን ይጠበቅበታል።

በአጠቃላይ የዉሃ ልማት ፈንድ ስራ አስፈጻሚው በ2015 በጀት ዓመት ያቀዳቸውን ዋና ዋና ተግባራት ለማሳካት የውሃ ልማት ፈንድ ቦርድ (እንደ አዲስ የሚቋቋም ከሆነ) የጽ/ቤቱ አመራሮችና ሠራተኞች በባለቤትነት የበኩላቸውን ከፍተኛ ጥረት ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው ከወዲሁ የጋራ ግንዛቤ ሊያዝ ይገባል። ከዚህ በተጨማሪም የዘርፉ የበላይ አመራርና የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት በቀደሞ ጽ/ቤቱ ዕቅድ ትግበራ ሂደት ላይ አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

## አባሪዎች

**ሰንጠረዥ** 1፡- **የስራ አስፈጻሚው የ**2015 **በጀት ዓመት የፊዚካል ስራዎች የድርጊት መርሃ ግብር ዕቅድ ማቅረቢያ ቅጽ**

**ሰንጠርዥ** 2፡- **የ**2015 **በጀት ዓመት የፕሮጀክቶች እቅድ ማቅረቢያ ቅጽ**